የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ

ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

ነሐሴ7 ቀን 2008

# ከኢሕብፓ በሃገራችን ወቅታዊ ሁኔታ የተሰጠ መግለጫ

## ጀግናውና ቆራጡ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!

የዘረኛውን ወያኔ አምባገነን የግፍ አገዛዝ ለማስወገድ ጀግናውና ሀገር ወዳድ ወገኖቻችን ለሃገራችሁ የምታደርጉት ታሪካዊ ተጋድሎና በጀግንነት የምትከፍሉት የህይወት መስዋትነት ሁሉንም ወገን የሚያኮራ ተግባር ነው። እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢሔራዊ ፓርቲ(ኢሕብፓ) አባሎች ከጎናችሁ ተሰልፈን የትግሉ አጋር ለመሆን አስፈላጊውን ትብብር: አስተዋጽዎና መስዋትነት ለመክፈል ቆርጠን ተነስተናል፡፡

ይህ ጎጠኛና ዘረኛ አስተዳደር በአማራው፣ ኦሮሞው፣ በኦጋዴንና ጋንቤላ ሕዝብ ላይ የሚፈጽመው አሰቃቂ እልቂትና ጭፍጨፋ እየተባባሰ

ሄዶ በተለይም በወልቃይትጠገዴና ቢኒሻንጉልን ሕዝብ የዘር ማጥፋት ዘመቻውንና እንዲሁም በኦሮሞ ሕዝብ ላይ የሚያካሂደው እብሪት የተሞላበት የግፍ ጭፍጨፋ ከምንጊዜውም ቀዳሚ ሥራዉ አድርጎታል፡፡

ይህ በዚህ እያለ በግፍ የተገደሉ ንፁሃን ዜጎቻችንን አስከሬን እንኳን አንስተን በአግባቡና በስነስርአት እንዳይቀበሩ በመከልከል በጢሻ፣ በሸለቆና ጉድጓድ ውስጥ እየጣሉ የጅብና ሌሎችም ዱር አራዊት መጫወቻ አድርጓል አሁንም እያደረገ ነው ወደፊትም ከማድረግ አይቆጠብም፡፡

የወያኔ ዘረኝነት፣ ጎጠኝነትና ጠባብነት የመጀመሪያና የመጨረሻው ተልዕኮው ነው፡፡ የመላው አለም ታሪክ ዘጋቢዎች በማህደራቸአው እንዳስቀመጡት ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ለብዙ ሽህ ዘመናት ነፃነቷን ጥብቃ እንደኖረች ገልጸዋል። የወያኔ ክህደት ባህሪውም ኢትዮጵያን የመቶ አመት አፈታሪክ ነው ከማለትም አላገደውም። በአንፃሩ እኛ ኢትዮጵያዊ ልጆቿ የጎሳ፣ የቋንቋና የባሕል ልዩነቶች የአንድነታችን መታወቂያ፣ጌጣችንና ክብራችን መሆኑን ለእነዚህ ዘረኛ አስተዳደር በሚገባቸው ቋንቋ እናረጋግጥለን።

እኛ ኢትዮጵያኖች በኢትዮጵያ አገራችን የምንመካ በኢትዮዊነታችን የምንኮራ እንጂ የእኛን ማንነት የማንም የባንዳ ልጅ ሊነግረን አይችእልም። ሁሉም ኢትዬጵያዊ በህብረት አንድነታችን ላይ በማተኮር በ ስቸኳይ ጥሪ ተደርጎ ከሕዝባችን ጎን በመሰለፍ የተቀጣጠለውን የሕዝብ አመፅና የትግል ነበልባል በበለጠ አጋይቶ ከግቡ ማድረስ አለብን ብለን እናምናለን። ለዚህም ጥሪ ፓርቲያችን የተቻለውን ሁሉ ለማድረግና መስዋትነትን ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን እናረጋግጣለን

**የተቀጣጠለው ትግል ተቀናጅቶ ይሰራ!**

**ድል የኢትዮጵያ ህዝብ ነው!**

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ (ኢሕብፓ)**

E-Mails: - nile@epnp.info

Nile.epnp@gmail.com

Web site: - www.epnp.info